
# ዜና ቤተ ክርስቲያን

ይህ ጋዜጣችን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ፤ ሥርዓትና ባህል ፤ ታሪክና ዜና የሚያትም ስለሆነ ዜና ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ተሰየመ ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፵፮ኛ ዓመት ቍ/፻፭፩ | አ/አ/ ጳጉሜን ፩ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ /ም | የጋዜጣው ዋጋ አንዱ 0.10 ለውጭ ሀገር ዕጥፍ ይሆናል ። | ስልክ ቍጥር 110099፳ የመልእክት ሣ/ ቍ/ 1283 |


## የአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት የሰላም ጥሪአስተባባሪ በጦርነት ለተጎዱ ወገኖቻችን ፫፻ሺህ ፱፻፶፫ ብር ረዱ



ቅዱስነታቸው የርዳታውን ገንዘብ ቼክ ባስረከቡበት ወቅት

በሀገራችን በመካኼድ ላይባለው የርስ በርስ ጦርነትና ድርቅ ባስ ከተለው ችግር ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው የሚገኙት ወገኖች ሰላም እንዲያገኙ የሻዕቢያና የወያኔ ቡድኖች ወደ ሰላም መድረክ እን ዲመለሱ የአዲስ አበባ አብያተ ክር ስቲያናት ጥሪ አስተባባሪ ።
በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬ ዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳ ሳት ዘኢትዮጵያ ሰብሳቢነት በመ ንበረ ፓትርያርክ ጽሕፈት ቤት የ ሰብሰባ አዳራሽ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የመ ምሪያ ኃላፊዎች የአዲስ [illegible] ገዳ ማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች የሰበካ ጉባኤ ምክትል ሊቃነመና

ተከታዩን በ፫ኛው ገጽ ይመልከቱ

## ፓትርያርኩ የአቦምሳን መልሶ ማቋቋሚያ መርቀው ከፈቱ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬ ዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳ ሳት ዘኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ኦር ቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአርሲ አስተዳደር በመርቲ ፲፩ አውራጃ በአቦምሳ ከተማ ያቋቋ መችውን የመልስ ማቋቋሚያ ፕሮ ጀክት ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፹፱

ተከታዩን በ፰ኛው ገጽ ይመልከቱ

## ብፁዕአቡነጎርጎርዮስዐረፉ

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የደቡብ ሸዋ ሊቀ ጳጳስ ሐምሌ ፳፪ ቀን ፲፱፻ ፹፱ ዓ/ም በመቂ ቅዱስ ሚካኤል ለሚገኙ ምእመናን የተለመደ አባ ታዊ ትምህርታቸውን ለመስጠት ሲኼዱ በድንገት በመኪና አደጋ ምክንያት በ፶ ዓመት ዕድሜያቸው



ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ እኋህ ነበሩ ።

ዐርፈዋል፤የቀብራቸውም ሥነ ሥር ዓት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆ ሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳ

ተከታዩን በ፪ኛው ይመልከቱ

## የበዓላትና የአጽዋማት መግለጫ

በቤተ ክርስቲያን የአጽዋማትና የበዓላት ሥርዓት ከፍና ዝቅ የሚልና ወጣ ወረድ የለበት መሆኑ በማንም በንድ ግልጽ ነው። የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣም ይህንኑ በመ[illegible] ዓመቱ የዘመን መለ[illegible]

www.ethiopianorthodox.org

# ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ . . .

ከ፩ኛው ገጽ የዞረ

ሳት ዘኢትዮጵያ፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣የደቡብ ሸዋ የኢሥፓ ዋናጸሐፊ ጓድ ዘካርያስ ናደው የደቡብ ሸዋ አስተዳዳሪ ጓድ ጴጥሮስ ወልታሞና ሌሎችም የመንግሥት ባለሥልጣኖች፣ብፁዕ ጴጥሮስ በኢትዮጵያ የግሪክ ኮሚዩኒቲ ጳጳስ ፣ ከአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት የመጡ ካህናትናምእመናን ጠቅላላ የዝዋይ ከተማና የአካባቢው እንደዚሁም ከ፭፻ በላይ የሚሆኑ የማሠልጠኛው ደቀ መዛሙርት በተገኙበት ራሳቸው ባሠሩት ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ መቅደስ ውስጥ ተፈጽሞአል ።

## የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ አጭር የሕይወት ታሪክ

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም በወሎ ክፍለ ሀገር በደሴ ከተማ ተወለዱ ወላጆቻቸው አቶ ገበየሁና ወ/ሮ አሰለፈች ካሣ ይባላሉ ። ዕድሜአቸው ለትምህርት እንደደረሰ በደሴ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ከንባብ እስከ ዜማ ከተማሩ በኋላ ወደ ላስታ ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ በመኼድ አባ ክፍሌ ከተባሉት መምህር የውዳሴና ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ፣ አዕማደ ምሥጢርና ባሕረ ሐሳብ ተምረዋል መምህር ክፍሌም ትምህርት አቀባበላቸውንና የያዙትን የማይገድፉ መሆናቸውን ይልቁንም ራሳቸው ከሚማሩት ጉባኤ አልፈው ከበላያቸው ያሉት ሌሎች ደቀ መዛሙርት የሚማሩትን በማዳመጥ ቀድመው ይዘው መገኘታቸውን በመመልከት ስማቸውን መዝገበ ሥላሴ ብለው ሠይመዋቸዋል ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መዝገበ ሥላሴ ክፍሌ እየተባሉ በመምህራቸው ስም ሲጠሩ ኖረዋል መዝገበ ሥላሴ የወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ዲቁና ተቀብለዋል ከዚያም በኋላ ወደ ሸዋ ክፍለ ሀገር መጥተው በደብረ ሊባኖስ በአቡነ ተ/ ሃይማኖት ገዳም ማዕረገ ምንኩስና ከተቀበሉ በኋላ ወደ አዲስ ዓለም ማርያም በመኼድ ከመምህር አፈወርቅ መንገሻ ቅኔ ከነ አገባቡ ጠንቅቀው አውቀዋል እንደገናም ወደ ደብረ ሊባኖስ በመመለስ የሐዲሳት ትርጓሜና ትምህርተ ሃይማኖት ከመምህር ፍሥሐ መጸሐፈ ሊቃውንት ከመምህር ቢረሳው ተምረዋል እንደዚሁም ወደ ደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ማርያም ኼደው ከመምህር ገብረ ሕይወት የሐዲሳት ትርጓሜን አደላድለው ተመርቀዋል በዚሁ ደብር የቅዳሴ ዜማን ከነሥርዓቱ አጠናቀው ተምረዋል ።

አባ መዝገበ ሥላሴ ክፍሌ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የቅስና ማዕረግ ተቀብለው በዚሁ ሙያቸው ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ወደ ሐረርጌ ክፍለ ሐገር ተልከው በሐረር ከተማ የ፩ኛና የ፪ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ፈጽመዋል ከዚህ በኋላ የቁልቢ ገብርኤል ገዳም አስተዳዳሪ በመሆን ለሁለት ዓመታት አገልግለዋል ።

አባ መዝገበ ሥላሴ በ፲፱፻፶፰ ዓ/ም ለከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ወደ ግሪክ አገር ተልከው በደሴቱ ፍጥሞ ለሁለት ዓመታት መንፈሳዊ ትምህርት ተምረው ዲፕሎማ ተቀብለዋል በአቴና ዩንቨርስቲ ለአራት ዓመታት የቲኦሎጂ ትምህርት ተምረው በማስትሬት ድግሪ (ኤም - ኤ -)ተመርቀዋል እንደገናም ለቋንቋ ጥናት ወደ ሲውዘርላንድ በመኼድ በፍሪቦንግ ዩኒቨርስቲ የፈረንሳይኛ ቋንቋ አጥንተው ዲፕሎማ አግኝተዋል ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ አባ መዝገበ ሥላሴ ወደ እስራኤል አገር ኼደው በኢየሩሳሌም በሚገኘው የኢትዮጵያ ገዳም በተለይ በደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ተቀምጠው በኢየሩሳሌም የሚኖሩ የኢትዮጵያውያን ልጆችን በመሰብሰብ የአማርኛ ቋንቋና ባህል መንፈሳዊ ትምህርት እያስተማሩ ለገዳሙም ገቢ ሊያስገኝ የሚችል የዕጣንና ከርቤ ቅመማ በመሥራት ለገዳሙ መነኮሳት ያሳዩ ነበር በዚህም ጊዜ በኢየሩሳሌም በሚገኘው በግሪክ ቴዎሎጂካል ኮሌጅ የዐረብኛ ቋንቋ አጥንተው ሰርቲፊኬት ተቀብለዋል ።

በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተ/ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ወደ አዲስ አበባ መጥተው በጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲያበረክቱ ቆይተዋል ።



ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ሞስኮ ውስጥ በተደረገው የሰላም ጉባኤ ከብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ጋር ተካፍለው ነበር

፱/ ከካሚመት እስከ ዕለተ [illegible]

አባ መዝገበ ሥላሴ [illegible]

ወደ ፮ኛው ገጽ [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

# ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ – – –

ከ፪ኛው ገጽ የዞረ

፲፱፻፷፩ ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አንብሮተ እድ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ጳጳስ ተብለው ተሾሙ ወዲያውም የቅዱስ ሲኖዶስ አባል እንደሆኑና የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ሆኑ ፤

የብፁዕነታቸው የሀገረ ስብከት ጽ/ቤት በወቅቱ በአዲስ አበባ ቢሆንም ለአስተዳደሩ ወሳኝና ቀልጣፋ መመሪያ በመስጠት አብዛኛውን ጊዜ በዝዋይ ካህናት ማሠልጠኛ ካህናትንና ደቀመዛሙርትን በማስተማርና የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በመሥራት ያሳልፉ ነበር ስለዚህም በዝዋይ ካህናት ማሠልጠኛ ውስጥ ከፍተኛ የሥራ ፍሬ አሳይተዋል ይኸው እንደሚከተለው የተዘረዘረው ነው ።

በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ርዳታ በደቡብ ሸዋ አስተዳደር በዝዋይ ተሠርቶ የነበረው መንፈሳዊ ት/ቤቱ የትምህርት ዓላማውን ሳይተው በገዳም ሥርዓት እንዲተዳደር በቅዱስ ሲኖዶስ አስወስነዋል ። ማሠልጠኛው ቀደም ብሎ ቢመሠረትም በውስጡ ካህናት የሚጸልዩበት የተማሪዎችም ተግባራዊ የሚያደርጉበት ቤ/ክ ባለመኖሩ ብፁዕነታቸው ከተረከቡት በኋላ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው የቅዱስ ገብርኤልን ጽላት አስገብተዋል ስሙንም ዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም በሚለት አሠይመውታል ። ገዳሙ እንደሌሎች የኢትዮጵያ ገዳማት የነግህና የሠርክ የሚገበር ጸሎት የሚደርስበት ከመሆኑ ጋር መነኮሳቱ በቀለምና በልዩ ልዩ ተግባረእድ ትምህርት ይሠለጥኑበታል ከሸዋ ሀገረ ስብከትና ከአርሲ ፣ ከሐረር ከሌሎችም ሀገረ ስብከቶች የሚላኩ ካህናት የስብከተ ወንጌልና የልማት ኮርስ ያጠናሉ ።

በዚህም መሠረት ገዳሙ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በማሠልጠኛው ውስጥ ፪ሺ፰፻ ካህናት ሠልጥነዋል ይህም ቁጥር የሚያመለክተው የአራትና የሦስት ወር ኮርስ የተከታተሉትን ብቻ ነው በአዳሪነት በገዳሙ ውስጥ እየኖሩ በቤተ ክርስቲያኖችን ትውፊት መሠረት የሀገራቸውን ትምህርት ንባ



ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ለተቸገሩ ወገኖች የቍሳቍስ ርዳታ ያደርጉ በነበሩበት ወቅት

ብና ቅዳሴ ፤ የእጅ ጽሑፍ ፤ የቅዱስ ያሬድን ጸዋትወ ዜማ ፤ ቅኔና አቋቋም የተማሩና የሚማሩ ደቀ መዛሙርት ፳፪ ናቸው ይህም ቁጥር የሚያመለክተው ብፁዕነታቸው የሚያሳድጓቸው እናትና አባት የሌላቸውን ቢኖራቸውም አስተማሪ ያጡትን ሕፃናት ጨምሮ ነው ። በገዳሙ ውስጥ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት በመከታተል በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ መዐረገ ምንኩስናን የተቀበሉና ከሌላም ገዳም መንኩሰው መጥተው በገዳሙ ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ገዳሙን በቀዋሚነት የሚያገለግሉ የገዳሙን ሥርዐት የሚጠብቁና የሚያስጠብቁ ፵፭ መነኮሳት አሉ ። ከላይ የተጠቀሱትንም የአብነት ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራንም ከነዚህ መነኮሳት መካከል ናቸው ።

ብፁዕነታቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ስብከት ዘዴ በቤተ ክርስቲያን

ተከታዩን በ፭ኛው ገጽ ይመልከቱ



ብፁዕነታቸው ለሠልጣኞች ካህናት የምስክር ወረቀትና ሽልማት ይሰጡ በነበሩበት ጊዜ

www.ethiopianorthodox.org

ከ፩ኛው ገጽ የዞረ

ታሪክና በጠቅላላ የሃይማኖት ትምህርት አሠልጥነው ለመምህርነት ያበቋቸው መምህራን አሥራ አንድ ናቸው እነሱም ፣

፩/ አባ ኃይለ ሚካኤል
፪/ » ማርቆስ ፣
፫/ » ኃይለ ኢየሱስ
፬/ » አብርሃም
፭/ መምህር ክፍለ ዮሐንስ (ንቡረ እድ)
፮/ ዲያቆን ታደሰ ፣
፯/ » ታሪኩ
፰/ » ሙሴ
፱/ » ኃይለ ኢየሱስ
፲/ » ጳውሎስ
፲፩/ » አበበ ናቸው ከእነዚህም መካከል ዲያቆናቱ በዩኒቨርስቲ ከፍተኛ ትምህርት የሚከታተሉ ሲሆኑ መነኮሳቱ በተለያዩ ቦታዎች ቤተ ክርስቲያናችንን በማገልገል ላይ ይገኛሉ ።

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ማሠልጠኛወን በሥርዓተ ገዳም እንዲተዳደር ካደረጉ በኋላ ቀድሞ ከነበሩት ቤቶች ሌላ ፣

፩ኛ/ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ከነሙሉ ድርጅቱ
፪ኛ/ አንድ የጥምቀተ ክርስትና ሥርዓት መፈጸሚያ ቤት
፫ኛ/ ሁለት የትምህርት መስጫ አዳራሾች
፬ኛ/ ፲ ክፍሎችና አንድ አዳራሽ ያለው እንግዳ መቀበያ ቤት ከተሟላ ድርጅቱ ጋር አሠርተዋል።

እንደዚሁም የገዳሙ አገልግሎት የተሟላ ይሆን ዘንድ ምንም እንኳ ቀደም ብሎ የጀኔሬተር መብራት የነበረ ቢሆንም አገልግሎቱ እጅግ አነስተኛ ስለነበር ከዝዋይ መብራት ኃይል በቀጥታ መብራት እንዲገባ ከማድረጋቸው ጋር ቴሌፎንም አስገብተዋል አንድ ከፍተኛ ኃይል ያለው ወፍጮ አስተክለዋል እንዲሁም በገዳሙ ላለው አትክልት የሚያገለግል አንድ የውሃ ሞተር አቋቁመዋል ።

ገዳሙ በማናቸውም በኩል ራሱን እንዲችል ብፁዕነታቸው የተለያዩ የልማት አውታሮችን ዘርግተዋል ከእነዚህም አንደኛው የልማት ክፍል የሚከተለው ነው ።

፩ኛ/ 200-000 የባሕር ዛፍ
፪ኛ/ 400 አርዘ ሊባኖስ
፫ኛ/ 8000 ትሪማንቲሪ
፬ኛ/ 12000 የሙዝ ተክል
፭ኛ/ 650 የብርቱካን ተክል
፮ኛ/ 436 የቡና ተክል
፯ኛ/ 300 የፓፓያ ተክል በገዳሙ ግቢ ውስጥ እንዲለማ አድርገዋል ከነዚህም ተክሎች ውስጥ ከቡናው በቀር ሁሉም ፍሬ በመስጠት ላይ ናቸው

ብፁዕነታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ራስዋን በራስዋ መርዳት እንዳለባት ሲያስተምሩ ሁልጊዜ የሚናገሩት ቃል ፈረንጆች ገንዘብ የሚሰጡን እራሳችንን እንድንችል ሲያስተምሩን ነው እንጂ ሊጠሩን አይደለም » የሚል ነበር ስለዚህም በሀገረ ስብከታቸው ውስጥ እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ራስዋን መቻል እንደሚገባት የዝዋይ ሐመረ ብርሃን ገብርኤል ገዳምን እንደ ሞዴል አቋቁመዋል ።

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በሀገረ ስብከታቸው ጽ/ቤት የአስተዳደር ሥራ እንዲሁም በገዳሙ ማሠልጠኛ ውስጥ ከላይ የተዘረዘረው ሰው መድረክ ፣

፬/ ትምህርተ ሃይማኖት(ዶግማ)
፭/ የስብከት ዘዴ(ኦርቶዶክሳዊ)
፮/ ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ
፯/ ሥርዐተ ፀሎት
፰/ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሲሆኑ ከ፩ - ፫ ተራ ቁጥር ያሉት ታትመዋል አምስቱ ግን ሕትመት ብቻ የቀራቸው ዝግጅቶች ናቸው ይሁን እንጂ ያልታተሙትም ቢሆኑ በብዙ ቅጂ እየተባዙ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ ባሉት ማሠልጠኛዎች ሁሉ በየጊዜው ለሚሠለጥኑ ካህናት መማሪያ ሆነው እያገለገሉ ናቸው ። ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት አስተዳደር ለአመራር አመቺ ይሆን ዘንድ የዐሥራ አንድን አውራጃዎች ሊቃነ ካህናት በዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም በዓመት ሁለት ጊዜ እየሰበሰቡ ሲሚናር በመስጠታቸውና የሰበካ ጉባኤው እስተዋጽኦ እንደሚገባ በመ



ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በማስተማር ገበታ ላይ

የሥራ ዓይነት ሁሉ ቢደራረብባቸው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ወንድሞቻችን ሆይ በቃላችንም ሆነ በመጽሐፋችን የነገርናችሁን አጽንታችሁ ያዙ» እንዳለ (፪ተሰ ፪ ፣ ፲፭) መልዕክታቸውን በቃልም በመጽሐፍም በልማት ሥራ አስተላልፈዋል በዚህም ረገድ ብፁዕነታቸው ፰ መጻሕፍት ጽፈዋል ።

እነዚህም የሚከተሉት ናቸው

፩/ መሠረተ እምነት
፪/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ
፫/ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓ

ሰብሰቡ በ፲፱፻፸፭ ዓ/ም በ፲፱፻፸፮ በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ ላይ አንደኛ በመሆን ሁለት ጊዜ ተሸልመዋል ፡

ብፁዕነታቸው በሸዋ ሀገረ ስብከት ውስጥ እየተዘዋወሩ ትምህርተ ወንጌልን ከማስተማራቸው የተነሣ በርከት ያሉ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት በዘመናዊ አሠራር ታንጸዋል ለምሳሌ ናዝሬት ቅ/ማርያም በደብረ ጽዮን ጥሙጋ አማኑኤል በስላሌ አራት ማርያም በወሊሶ ማዮን ገብረ መንፈስ ቅዱስ በአንቦ ጉደር ቅ/ገብርኤል በባኮ

ተከታዩን በ፱ኛው ገጽ ይመልከቱ

www.ethiopianorthodox.org

# ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ . . .

ከ፰ኛው ገጽ የዞረ

ቅዱስ ሚካኤልና የመሳሰሉትን አሠርተዋል ፤ ከዚህም ጋር ያረጁ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታደሱና እንዲጠገኑ አድርገዋል ።

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በዐሥራ አንድ ዓመታት ውስጥ ከዚህ በላይ ባጭሩ የተገለጠውን መንፈሳዊ የሥራ ፍሬ አሳይተዋል ።

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ እንደ ጎርጎርዮስ ዘአርማንያ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክር በትምህርታቸውና በስብከታቸው በድርሰታቸውና በሌላውም ሥራቸው ሁሉ «ከዋክብ ብርሃን» ነበሩ።

ብፁዕነታቸው በዕውቀታቸውበ ቋንቋ ችሎታቸውና በንግግር ስልታቸው ቤተ ክርስቲያናችንን የሚወክሉ ዓለም አቀፍ ሰው ነበሩ ፤ በመሆናቸውም ቤተ ክርስቲያንን በመወከል ብዙ ጊዜ በዓለም አቀፍ ጉባኤዎች እየተገኙ ስለ ቤተ ክርስቲያን ተወያይተዋል ጽሑፍም አቅርበዋል ።

የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ታላቅ ሰውነት ከሀከር ውስጥና ከሀገር ውጭ ባገኙት ዕውቀት ብቻ አልነበረም ልዩ ልዩ የንግግር የስብከትና የማስተማር ስጦታ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ታላቅ አባት ነበሩ በዚህም ስጦታቸው ቤተ ክርስቲያኒቱ ያጣቻቸውን ታላላቅ ሰዎች ወክለው የምእመናንን ልብ የሚያጽናኑ አባት ስለነበሩ ቤተ ክርስቲያናችን እኒህን አኩሪና መመኪያ ባጭር ጊዜ ምትክ የማይገኝላቸውን ታላቅ አባት በማጣትዋ ኀዘንዋ እጅግ ከፍ ያለ ነው ።

# ስለ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ዕረፍት የተደረሱ ቅኔያት

### ፩/ ጉባኤ ቃና

ዝዋይ ኀደግነ እምእሉ ፈደላትኪ ሠለስቱ
አሐደ ፈደለ ለጎርጎርዮስ በሞቱ ።

### ፪/ ሠላሴ

ጎርጎርዮስ አይቴኑመ ፍቁረ ልብከ አፈወርቅ
ዘትሰምዮ መንከረ በዘትርጓሜሁ መልእክት
በፍኖት እስመ ኢያውገዞ ለመልአከ ዘሞት
እስከ ለብዙኃን ትፈጽሞ ነሢአ ሐዲስ ልደት
ወእንዘ አፈወርቅ በትምህርት
አፈወርቅ ዘጸልዐ ቃለ ኀዘናት
ለሕዝብከ ትነግር ለምንት ።

### ፫/ ግእዝ ዕጣነ ሞገር

እመ በወርኀ ዘርኡ ይነውም
ወእመ ገራህቱ የኀድግ ሐራሲ
በዕርፈ መስቀል ጎርጎርዮስ ፤
ኢይሰመይ ዐብደ ትድመ እግዚኡ ክርስቶስ ፤
ለፈጽሞ ግብሩ ብዙኀ በመጠነ ዕድሜ ንኡስ ፤
ጎርጎርዮስ እምጣነ ፀመደ ዕምደ ምእት ሐምስ ፤
ዲበ ጠረጴዛ ዘወርቅ ማርያም
በዕለተ ትቄድስ ኢየሱስ ፤
ጎርጎርዮስ ይኩን ተራዳኤ
ዘምስለ ጴጥሮስ ቀሲስ ፤
ጎርጎርዮስ እስመ ይመስሉ ለጴጥሮስ ።

### ፬/ ዕዝል ዕጣነ ሞገር

እግዚአብሔር ካህን ዘሥልጣንከ ክቡር ፤
ገባሬ ሠናይ ዘኮነ ከመ ትግበር ፤
ከመስ ኢትትናገር ፤
ቅዳሴ ካልእ ጎርጎርዮስ በዘገብርኤል መንበር ፤
ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ሊቀ ቀዳሚ በነገረ ኩሉ ምሥጢር ።
ኢኮነ ሆሣዕና እብ ጎርጎርዮስ ጎር ።
ነጊሤ ግዕጠንት ዘወርቅ ጎርጎርዮስ ፤ ካህነ ሰላም ወፍቅር
ለምንት ጉንደየ ባሕቲቱ
ውስተ ቤተ መቅደስ ንኪር ፤
እስመ ይጸገሐዎ ማኅበር ፤
ቀዊሞሙ አፍአ እምድኅረ መዝሙር ፤
ግዕመ ቃሉ ይሰምዑ ለምክር ።

መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

### ጉባኤ ቃና

ናውጽእ እንከ እም ውስተ ልብነ ጻዕቀ ፤
ሞተ አቡሁ ቅዱስ እኮኑ በሞተ ወልዱ ተአውቀ

ተከታዩን በ፲ኛው ገጽ ይመልከቱ

እንኳን ከዘመነ ማርቆስ ወደ ዘመነ ሉቃስ
በሰላም አደረሰዎት

### መልካም አዲስ ዓመት

በዚህ እትም የሐምሌና የነሐሴ ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ተጠቃሎ የወጣ መሆኑን ለደንበኞቻችን እንገልጻለን ።

የዝግጅት ክፍሉ

www.ethiopianorthodox.org

## ሰለብዑሰ አቡነ ጎርጎርዮስ - • •

ከ፱ኛው ገጽ የዞረ

### ፩ ሥላሴትኔ

እም አቤል ቀዳማዊ ዘትገፍዑነ ዲበ ምድር
መቃብር ወሞት አዕራረ ሊቃውንት አእጹቅ ፤
ሰሊክሙ እመ ተሐድገ ርእሰ ለሊት ፤
እም ዘመነ አዳም ወሔዋን ምስለ አዕሩግ ወደቅ ፤
ዘገበርክምዎ በበሕቅ ፤
አመፃ ይትሐደግ በዘየሐልቅ ፤
እስመ ጽድቅ ቤዛሁ ለጽድቅ ።

### ፪ ሥላሴ ቅኔ

መጻሕፍት ዘሐዲሳት ፤ ለርእሰሙ ግብሩ ዘተናገሩ ፤
ወእለ ይቤሉ ለነ ለውሉደ ሰብእ ቀዲሙ ፤
ኢትዝግቡ በመልዕልተ ምድር መዘገበ ለክሙ ፤
ዳእሙ ዝግቡ መዝገበ ሰማይ አንትሙ ፤
እንዘ ይፈትሑ በርእሶሙ ፤
እስመ ዘትጽሕፈ ቃለ ከመ ይፈጽሙ ፤
መዝገበሙ በሰማይ አቀሙ ።

### ፩ መወድስ ቅኔ

መጻሕፍተ ሥርዓት ወሕግ ወአሚነ ተሰፉ ፤
ዘበበጊዜሁ ተጽሕፉ በልሳነ ኮሉ ብሔር ፤
ይቤሉነ ለነ በቃለ ተግሣጽ ወምክር ፤
ኢንወርድ ኀበ ተሰቀልነ እመኒ ለክብር ፤
ወሚመ ለሐሳር ፤
ወኢታውጽኡነ እንከ እምዘዚአነ ማኅደር ፤

#### ለዓለም

ከመ ጎርጎርዮስ ማእምርነ ወፍቁ ርነ በግብር ፤
ዘያነብበነ በለብዎ ወይሜህረነ በምሥጢር ፤
እስከነ ተንሥአ ለነ በላእለ ይእቲ ምድር
ድኅረ ጎርጎርዮስ ከመ ሙሴ አምጣነ ትኄይስ መቃብር ።

### ፪ ኩልክሙ መወድስ ቅኔ

ጎርጎርዮስ አብ ካህነ ዓለም ፤
በዕለተ ሰንበት ቅድስት እረፍተ መዋቲ ሥጋከ ፤
አመ በፍኖት ሞተ ኪዳነ አቤል አብጻሕከ ፤
ዲያቆናት ፪ቱ ይቤሉ ኪያከ ፤
እስመ ሐልቀ ሰአትከ ፤ ምስለ ፪ቱላእካን እንዘ በፍኖት አዲከ ፤

#### ለዓለም

ትቤሰይሂ ፍሬ ጻማከ ፤ በዘአክሊለ ክብር ሐሠሥከ ፤
ገመርሕበ አቤል ሞተ ሥጋ ሩጸተሀገር እመ ወጠንከ ፤
፪ቱ አበው እለ ቀደሙከ ፤
እመ ይረውጹ በቅድሜከ ኢያምሰጡ እምኔከ ፤
እስመ እሙንቱ በእግር ወበ ሠረገላ ለሊከ ።

### ፫ መወድስ ቅኔ

ከመ አርዌ ምድር ኮነት ወከመ ውህጠታ ፤
ለበትረ ፪ቱ ኢያኔስ ወኢያንቤሬስ ካልእታ ፤
በትረ እደ ሙሴ ነቢይ ጊዜ ለምድረ ግብጽ ፀአታ ፤
ለሊቀ ጳጳስ በትረ እዴሁ ፤
አርዌ ምድር አምጣነ ኮነቶ በብዙኅ መቅሰፍታ ፤
ወውህጠቶ ለባህቲታ ፤
እንዘ ለሊሁ ውእቱ ቢሳየ እኀልዘማውታ ፤

#### ለዓለም

ኣመ ፈነዎሙ በበ፪ ለዓለመ ሥጋ ውስቴታ ፤
ከመ አዘዞሙ እግዚእነ ለሐዋርያት በኃልጎታ ፤
ኢትንሥኡ በትረ ለእደዊከሙ መንገታ ፤
አበዊነ ለምሀር እንዘ ተሐውሩ በበ ጾታ ።

መ/ ም/ መ/ ሩፋኤል ፈታሒ

www.ethiopianorthodox.org

# ስለ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ – –

ከ፲ኛው ገጽ የዞረ

ጉ ባ ኤ ቃ ና

አይቴ የሐውር ጎርጎርዮስ እንዘ ይቀርብ ቅድምና
ምውት እንተ ይበልእ ሞተ አቤል መና ።

ዘአምላኪየ

በምንት ተአርገ መንገለ ሰማይ ዘአልፋ ፤
ሕይወትከ ንስረ ሰማያት ዘተሰብረ ክንፋ
በእብነ ቤቱ ለአቤል አኮኑ ፤ አእጋሪሃ ተአቅፋ ።

ሥላሴ

ጎርጎርዮስ መጠንከ ቀናኤ ሃይማኖት ዘአበዊሁ ፤ አመኒ ሀገረ ዘደማ
ስቆ አልጸቀ ፤
ሳውል ጣዕመ ሕይወትከ በፍኖት ወድቀ ፤
ምረረ ሞቱ መብረቅ አምጣነ ግብተ በረቀ ፤
ወምስለ ጥምቀት ከመ አጽደቀ ፤
ሙሴ ሞትከ አበዊነ ሕቀ ፤
በደመና ወበባሕር አጥመቀ ።

ዕጣነ ሞገር

ጎርጎርዮስ አብ እንተ የአምር ብሉየ ፤
ቃለ መጻሕፍት ሰአረ ወአናህሰየ ፤
 በሰንበት ወበክረምት እስመ ጉያሁ ረሰየ ።
 ወአእይንቲነ ዘሌለየ ፤
ፈለገ መቃብር ምድያም አኮኑ ለአእይንቲነ ሕየ ፤
ጌዴዎን ዕለተ ሕልፈቱ ፈተናሙ ማየ ።
እምዘ በአምላክ ፈታሕነ እሞተ ሙሴ ፤
 ሞተ ጎርጎርዮስ አብየ ፤
እስመ ዘከማሁ አንስአ እምአኃዊሁ ነቢየ ፤
ወለ ጎርጎርዮስ ኢኃለየ ፤
ወሐመረ ብርሃን ግብፀ እምዙሉ ጌገየ ፤
እስመ ጾመ ረሰየ ቀላየ ።

መሪጌታ ቀፀላ መንግሥቱ፡

ጉባኤ ቃና

መቃብር ወሞት ላእካነ አቤል መቅደስ
ሥልጣነ ክህነት ተወክፉ እምነ አሐዱ ጳጳስ

፩/ ዘአምላኪየ

በቤተ መቃብር ተሠርዓ ማዕደ ሥጋ ወአጽም
በሰንበት አምጣነ ተፈትሐ ጎርጎርዮስ ጾም
ዘቦቱ ይሰረይ ፅማዌ ፤ ጌጋየ ኩሉ ዓለም

፪/ ዘእምላኪየ

ሐዋርያ ፍኖት ኮርስ ማእከለ ፍኖት ያስቆቁ
በፍኖት እስመ ተፈጸመ ጎርጎርዮስ ዕንቁ
እንዘ ሕሊናሁ ብዙኃ ለእለ በዝጉ ደቂቁ

፩/ መወድስ

ዕዝራ ወሄኖክ ዘተበአስዎ
እመ አምሰጥዎ ሞት ጸላኤ ሕይወቱ ለኤልያስ ፡
መአቶ አቁረረ በጎርጎርዮስ ፡
አምጣነ ተረክበ ቅድመ ገጹ
ጎርጎርዮስ ተአዛዚሆሙ ለዘኖኅ አልባስ ፡
ወበ ልሳነ ኤፍሬም ተተርጕመ ፤ መልእክተ ፡
ጳውሎስ ሞት ዘጸሐፈ ጳውሎስ ፡

ተከታዩን በ፲፪ኛው ገጽ ይመልከቱ

www.ethiopianorthodox.org

# ሰሞ ባለ?. ቅኔያት

ከ፲፩ኛው ገጽ የዞረ

ለዓለም

ምትሂ ወሙ ቆብር እእርከተ መርአዊ ሐዲስ ፣
በሠረገላ ይቀልሙዎ ለመርአዊ ሰላም ሊቀ ጳጳስ ፣
እንዘ ለከኛዱ ፆርማው ወርቀ ድንግልና ተርሴስ ፣
እንቀሰፎር እርእያሁ ወአምሳሊሁ አርማስቆስ ፣

መወድስ

ተሰዶተ አዳም ወሂዋን እምገነተ ተድላ ፣
ለእመ ይእዜ ይከውን ተአምረ እምኢኮነ
እምድኅረ ዘተድላ ገነተ በቀዳማዊ ኃጣእን
እስመ በጎርጎርዮስ ዶሐራዊ ፣
ዘትመስል ገነተ ፍስሐ ገነተ ረከብነ ፤
ወውስተ ገነቱ እስተጋብአ ፣
ልዑላነ ሰብእ ወሰብአ ትሑታነ ፣

ለዓለም

ለገነትሂ ተፈጥሮታ ለእመ በጽድቅ ሐተትነ ፤
ገነተ ፍስሐ እመ ፈጠረ ኢጸመወ እግዚእነ
ጎርጎርዮስ ገነተ በጊዜ ፈጠረ ለነ ፣
ደከመ በአውሮፓ ከመ ጽንእ ፍቅሩ ያጠይቀነ ፣

እሸቱ ዓለማየሁ
በዝዋይ ክህናት ማሠልጠኛ የቅኔ መምህር

## በመኪና እለፉ

ዝዋይ መቂ ደርሶ በጊዜ ለመግባት እየተጣደፉ
ብፁዕ !! - (አባ) ጎርጎርዮስ በሚያስደንቅ ፍጥነት በመኪና አለፉ ፤
ብሎ በሰጠው ቃል ሑሩ ወመሀሩ
የሐዋርያትን ትእዛዝ ሲያስከብሩ
ወይ አልመለስም ብለውም ሳይነግሩ
በዚያው በኼዱበት በዋሉበት ቀሩ
የዝዋይ የመቂ የፍተሻ ኬላ
ቀማኛ በዛበት ቁጥጥሩ ላላ
በጣም ያሳዝናል ተራውን ሰው አልፎ ጳጳሱን ሲበላ
በወርቅ በብር መስቀል ለሕዝበ ክርስቲያን
ቡራኬ እንዳልሰጠ ፤
ሐዲሱን ብሉዩን እንዳልፈተተበት እያገላበጠ
ጽሕፈቱን ፤ ድጉሰቱን በኅብረ ቀለማት እንዲያ እንዳላስጌጠ
ከመጻፊያ ሁሉ እርሱን የመረጠ
ሙያየ ነው ብሎ በፍጥነት ተቻኩሎ
መልካሙ ጣትዎ መቃብር ጨበጠ
ብፁዕ አባታችን ፍጥረት ሁሉ አማዎት
ቸኩለው ከበሩ
ይህንን ትሩፋት ይህንን በረከት
ከመቸው አኖሩ
በሃምሳ ዓመት ዕድሜ ምድር ቤት አፍርሰው
አዲስ ቤት የሠሩ
ሰፊ አዳራሽዎ ምን ጊዜ ተሠርቶ በፍጥነት አለቀ
የኛ ዳስ ገና ነው መቸ ተጠናቀቀ
የተመረኮዙት ሲሰበር ዘንግዎ
መናገር ሲሳነው አርምሞ ድምፅዎ ፤
አወይ አለማፈር ቁመን አየነዎ
በሉ እርስዎም ሂዱ እኛም ወደዚያው ነው
ዱሮም መንገደኛ ፊትና ኋላ ነው ።

ኤያሌው ገሠሠ መምህር ከአዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org